Legacy International Spiritual Ministry

2020 GC Annual Summary Report

Legacy International Spiritual Ministry
P.O.Box 192/1070
Cell # 251 930 651943
Act: #; Berhan Bank 2600010008458
Addis Ababa, Ethiopia

ለዉድ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ደጋፊዎች!

ጉዳዩ፡ የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2020 ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ

ሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት የአራተኛ ዓመቱን ሲያጠቃልል ለሌጋሲ ሥራ አመራር ቦርድ ሪፖርት እንደተደረገው፣ የአገልግሎቱ ዘመን ከኮቪድ-19 መከሰት የተነሳ ከባድ ተግዳሮት የነበረበት ቢሆንም የተፈጠረዉን የመዘጋጋት ሁኔታ (Lock Down) እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሰፊ የሶሻል ሚዲያ አገልግሎት እንደተከናወነ ነዉ፡፡ በመሆኑም አገልግሎቱ በተለይ ስድስት ወራት በነበረዉ መዘጋጋት ወቅት የበለጠ ዓለም አቀፋዊ እይታ እንዳገኘ እሙን ነዉ፡፡ በኢትዮጵያ ኮቪዱ ወራርሺኝ መግቢየ ላይ በነበሩ የሥልጠና እንቅስቃሴዎች ከበፊቶቹ ዓመታት ብዙ ያልተናነሰ ዉጤት ተመዝግቧል፡፡

በአሉታዊ መልኩም ሲታይ የአገልግሎቱ ቦርድ ወቅታዊ መሰባሰቦችማ ሆነ ጠቅላላ ጉባዔ በጊዜዉ ማድረግ ያልተቻለ ሲሆን ቦርዱ እአአ የ2020 ሥራና ሂሳብ እንቅስቃሴ ማየት የቻለዉ እአአ 2021 ከገባ በኋላ ዓመቱን አጠቃልሎ ነዉ፡፡ ሆኖም ባብዛኛዉ በየሳምንቱ ሐሙስ ማለዳ በነበረዉ የፀሎት መረብ በታቻለ መጠን ከቦርዱ አባላትና ሌሎች ተካፋዮች ጋር በመንፈስ ህብረት ለመገናኘት ጥረት ይደረግ እንደነበር ነዉ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ በጎ ፈቃደኞች፣ በጊዜያቸው፣ በዕውቀታቸውና በሀብታቸው ከአገልግሎቱ ጎን በመቆማቸዉ አመርቂ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በዓመቱ በታቀደዉ መሠረት የአገልግሎቱ አንኳር ተግባር የሆነዉ ሥልጠናን የመስጠት ሥራ ለሚመለከታቸዉ ተደራሾች በተለያዩ አካባቢዎች በመከናወኑ ወደ 85% ዉጤት ታይቷል፡፡

ክፍል አንድ - በግንባር የተሰጡ ሥልጠናዎች

ሀ. የወጣቶች ሥልጠና አገልግሎት

1ኛ ሃዋሳ ላይ የተደረገዉ ወጣቶች ሥልጠና የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር በሚለዉ ላይ ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህ ወጣቶቹ ከኔታ ጋር ያላቸዉን ቁርኝት መለማመድ እንድችሉና ሌሎችም እንድያስተላልፉ ነዉ፡፡ የየዕለት ግል ጊዜ ከጌታ ጋር ሥልጠና ለሶስት ግማሽ ግማሽ ቀናት፣ ከየካቲት 6-8፣ 2012 (February 14-16, 2020) የተካሄደዉ ከደቡብ ሪጂን ዩኒቬርስቲዎች ለተዉጣጡ **79** የክርሰቲያን ተማሪዎች ህብረት መሪዎች ሆኖ ከኢትዮጵያ የክርሰቲያን ተማሪዎች ህብረት አገልግሎት (EVaSUE) ጋር በመተባበር **በአሠልጣኞች ሥልጠና ስልት** ነዉ፡፡ **በሥልጠናዉ ወቅት የቅድመና የድህረ ሥልጠና ግብረ መልስ አሰሳ ተደርጎ ስለነበረ ትንተና ተደርጎበታል፡፡** ዉጤቱ **በጥቅሉ** እንደሚያሳየዉ ከሥልጠናዉ በፊት **ከ75** ግብረ መልስ ሰጪዎች መካከል **40ዎቹ** (53%) የጥሞና ጊዜ እንደነበራቸዉ የተገለጸ ሲሆን፣ ከሥልጠናው በኋላ የጥሞና ጊዜ ወደፊት ይኖረናል ያሉት ብዛት ደግሞ **60%** ነዉ፡፡ ይህ የሚያመለክተዉ ወጣቶቹ የጥሞና ጊዜ ለመዉሰድ ዉሳኔ ያደረጉት **በ7%** ከፍ እንዳለ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ **ከ75** ግብረ መልስ ሰጪዎች መካከል **18ቶቹ (24%)** ከሥልጠናዉ በፊት የጥሞና ጊዜ ምን እንደሆነ አናዉቅም ያሉ ሲሆን፣ ከሥልጠናዉ በኋላ ደግሞ **30%** በጥቅሉ ዕዉቀት እንዳገኙ ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ዕዉቀት የለንም ካሉት ሌላ ወደ **6%** የሚሆኑ ሌሎች ተጨማሪ ዕዉቀት ማግኘት መቻላቸዉን ነዉ፡፡

የደቡብ ክልል ዩኒቬርሲቲዎች ሠልጣኝ ክርስቲያን ተማሪዎች

2ኛ የነቀምት ወጣቶች ሥልጠና በወጣቶች ተግዳሮቶችና በአእምሮ መንፈስ መታደስ ርዕሶች ላይ የካቲት 14፣ 2012 (February 22, 2020) ተካሂዷል፡፡ ሥልጠናዉ በተከታታይ በሁለት ክፍለ ጊዜ የተሰጠ ሲሆን፣ ትኩረቱ ላይ ነበር፡፡ ሥልጠናዉን የተካፈሉት **47** ወጣቶች ናቸዉ፡፡
በነበረዉ የቤተ ክርስቲያኒቱ እሁድ አምልኮ ላይ (የካቲት 15፣ 2012) ለልጆችና ለወጣቶች በጉባኤ ላይ በትኩረት ተጸልዮላቸዋል፡፡

የነቀምት ሙወ ቁ 1 ሠልጣኝ ክርስቲያን ወጣቶች

የባኮ ዶንጎሮ ሙወ ሠልጣኝ ክርስቲያን ወጣቶች

3ኛ የባኮ ዶንጎሮ ሙሉ ወንጌል ወጣቶች ሥልጠና

በወጣቶች ተግዳሮቶችና በአእምሮ መንፈስ መታደስ ርዕሶች ላይ ያተኮረ ሆኖ፣ የተካሄደዉ የካቲት 21፣ 2012 (February 29, 2020) ለግማሽ ቀን ነዉ፡፡ ሥልጠናዉን የተካፈሉት ወጣቶች **ቁጥር 135** ነዉ፡፡ የሥልጠናዉ ተካፋዮቹ ከሌሎች ሙሉ ወንጌል አጥቢያዎችና ህብረቶች እንዲሁም ከመካነ የሱስ እንዲሁም፡ በአካባቢዉ ከሚገኝ ልጆች ማሳደጊያ ማዕከል የመጡም ነበሩ፡፡

ለ. የመሪዎች/አገልጋዮች፣ የወላጆችና ባለትዳሮችሥልጠና

1ኛ ከነቀምት ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን (ቁጥር 1) ጋር በመተባበር የተለያዩ ሥልጠናዎች የተካሄዱት **ከየካቲት 12-15፣ 2012 ዓ.ም. (February 20 - 23, 2020)** ባለዉ ጊዜ ነዉ፡፡ የሥልጠናዉ ተካፋዮች በተወሰነ ደረጃ ከሌሎች ሙሉ ወንጌል አጥቢያዎችም ነበሩ፡፡ ሥልጠናዉ ባብዛኛዉ በትርጉም (ከአማርኛ ወደ ኦሮምፋ) የተከናወነ ሲሆን ለወላጆች በኦሮምፋ በቀጥታም ተላልፏል፡፡
የመሪዎችና አገልጋዮች ሥልጠና የካቲት 12 እና 13፣ 2012 በሁለት ክፍለ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን የተካፈሉት በከፍተኛዉ ቁጥር **44 ሰዎች** ናቸዉ፤ የሥልጠናዉ ትኩረት **እግዚአብሔርን የማይፈራ ትዉልድ እንዳይነሳ** ተግቶ ስለመሥራት እና **አገልጋይነትና አገልግሎት ህይወት** ላይ ያተኮረ ነበር፡፡
ባለትዳሮችን ጨምሮ የወላጆች ሥልጠና የተካሄደዉ ከየካቲት 12-15፣ 2012 ዓ.ም. (February 20 - 23, 2020) ነዉ፡፡ በተለያዩ ሶስት ክፍለ ጊዜያት (ከየሰዓት በኋላ) የተሰጡት ሥልጠናዎች **የጋብቻ ትምህርት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ፣ የወላጅነት ሰባቱ መንፈሳዊ ምሰሶዎች** ናቸዉ፡፡ ሥልጠናዉን የተካፈሉት በከፍተኛዉ ቁጥር **173 ሰዎች** ናቸዉ፡፡
በዚሁ አጋጣሚ በእሁድ ስብከት ለማገልገል ዕድል ማግኘት ተችሏል፡፡

የነቀምት ሙወ ቁ 1 ሠልጣኝ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች

ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነ ዉ፡፡

የነቀምት ሙወ ቁ 1 ሠልጣኝ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች

የነቀምት ሙሉ ወንጌል ቁ 1 ሠልጣኝ ወላጆችና ባለትዳሮች

2ኛ ከባኮ ዶንጎሮ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክርስቲያን (ቁጥር 2) ጋር በመተባበር የተለያዩ ሥልጠናዎች የተካሄዱት **ከየካቲት 20 - 22፣ 2012 ዓ.ም. (February 28 - March 1፣ 2020)** ነዉ፡፡ የሥልጠናዉ ተካፋዮች በተወሰነ ደረጃ ከሌሎች ሙሉ ወንጌል አጥቢያዎ፣ ቤተ እምነቶችና ድርጅቶችም ነበሩ፡፡ ሥልጠናዉ ባብዛኛዉ በትርጉም (ከአማርኛ ወደ ኦሮምፋ) የተከናወነ ሲሆን ለወላጆች በኦሮምፋ በቀጥታም ተላልፏል፡፡

የመሪዎችና አገልጋዮች ሥልጠና የካቲት 20፣ 2012 (February 28, 2020) በአንድ ክፍለ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን የተካፈሉት በከፍተኛዉ ቁጥር **26 ሰዎች** ናቸዉ፤ የሥልጠናዉ ትኩረት **እግዚአብሔርን የማይፈራ ትዉልድ እንዳይነሳ** ተግቶ ስለመሥራት ነዉ፡፡ የተካፈሉት በባኮ ካለዉ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን (ቁጥር 1) ጭምር ነዉ፡፡

የወላጆች ሥልጠና የተካሄደዉ ከየካቲት 21-22፣ 2012 ዓ.ም. (February 29 - March 1፣ 2020) ነዉ፡፡ በተለያዩ ሁለት ክፍለ ጊዜያት (ከየሰዓት በኋላ) የተሰጡት ሥልጠናዎች **መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ እና የወላጅነት ሰባቱ ምሰሶዎች** ናቸዉ፡፡ ሥልጠናዉን የተካፈሉት በከፍተኛዉ ቁጥር **99 ሰዎች** ናቸዉ፡፡ የሥልጠናዉ ተካፋዮች ከሌሎች ሙሉ ወንጌል አጥቢያዎችና ህብረቶች፣ ከመካነ የሱስና መሠረተ ክርስቶስ ነበሩ፡

በነበረዉ የቤተ ክርስቲያኒቱ እሁድ አምልኮ ላይ የካቲት 22፣ 2012 ለልጆችና ለወጣቶች በጉባኤ ላይ በትኩረት ተጸልዮላቸዋል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ በእሁድ ስብከት ለማገልገል ዕድል ተገኝቷል፡፡

የባኮ ዶንጎሮ ሙ ወ ወላጆች በሥልጠና ላይ

ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነ ዉ::

3ኛ ከ-የምሥራች ወንጌል ለህዝቦች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን (አዲስ አበባ) ጋር በመተባበር የአንድ ቀን ወላጆች ሥልጠና የተካሄደዉ መጋቢት 12፣ 2012 (March 21፣2020) ነበር፤ ሥልጠናዉ የተሰጠዉ **በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ እና የወላጅነት ሰባቱ ምሰሶዎች** ላይ ነዉ:: ሥልጠናዉን የተካፈሉት ከሰዓት በፊትና በኋላ በከፍተኛዉ ቁጥር **31 ሰዎች** ናቸዉ::

ይህ ሥልጠና የተካሄደዉ ኮቪድ 19 በመንግሥትና በህዝብ ደረጃ ትኩረት ማግኘት ከጀመረ በኋላ ነዉ:: የሥልጠናዉ ተካፋዮች በማህበራዊ ርቀት የተቀመጡ ነበሩ::

የሁሉም ሥልጠናዎቹ ማጠቃለያ

በጥቅሉ በ2020 በጀት ዓመት **70** መሪዎችና አገልጋዮች፣ **261** ወጣቶች፣ በወላጅነት ሥልጠና ላይ **303** ተሳታፊዎች ሥልጠና እንደ ወሰዱ፣ በድምሩ በ4 ጣቢያዎች **634** ሠልጣኝ ተሳታፊዎች እንደነበሩና ይህ ለዓመቱ ከታቀደዉ 745 ጋር ሲነጻጸር **85%** ከንዉን ያሳያል::

ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነ ዉ::

ክፍል ሁለት - በማህበራዊ ሚዲያ የተከናወኑ አገልግሎቶች

ሀ. ወላጆችና ወጣቶችን በተመለከተ የፌስቡክ መልእክቶች

1ኛ ለወላጆች ጽሑፍ መልእክቶች

ለወላጆች የሚሆኑ አጫጭር በአማርኛና በኦሮምፋ የተዘጋጁ የፌስቡክ ጽሑፍ መልእክቶች ከኖቬምበር 2019 ጀምሮ መለጠፍ የተጀመረ ሲሆን፣ መሪ ቃል **በልዩነት የተገለጠ ወላጅ** የሚል ነዉ::

በዚሁ መሠረት **በአማርኛ ቋንቋ** ለ10 ሁለት ሁለት ሳምንታት በጥቅሉ 20 ሳምንታት ከ November 2019 ጀምሮ እስከ June 2020 (የኮቪድ 19 ወራት ጨምሮ) በፌስቡክ የተለጠፉት ወላጆች መልእክቶች **በ 23811 ሰዎች** ተጎብኝተዋል:: ቀደም ብሎ በ2019 ከነበሩት አራት ሳምንታት በስተቀር ይህ የተከናወነዉ ባብዛኛዉ እአአ 2020 ነዉ::

በፌስ ቡክ መለያ ቁጥሩ FBP #21 የሆነና **በልዩነት የተገለጠ ወላጅ ለህይወት መቀጠል ምክንያት ነዉ** የሚል በመሳፍንት 13፡7 ላይ ተመሥርቶ Jan 9, 2020 የተለጠፈዉ መልእክት ከፍተኛዉን እይታ አግኝቷል፣ ማለትም **በ 21518** ሰዎች ተጎብኝቷል::

በተመሳሳይ **በኦሮምፋ ቋንቋ** ቀደም ብሎ ለ5 ሁለት ሁለት ሳምንታት በጥቅሉ 10 ሳምንታት ከ December 2019 እስከ Feb 5, 2020 በፌስቡክ የተለጠፉት የወላጆች መልእክቶች **በ 233 ሰዎች** ብቻ ተጎብኝተዋል::
በጥቅሉ በአማርኛም ሆነ በኦሮምኛ ቋንቋ **የተለጠፉ አጫጭር የወላጆች ጽሑፍ መልእክቶች** ከጅማሬዉ **በ24044 ዲጂታል** ተመልካቾች (ሰዎች) ተጎብኝተዋል::

የምሥራች ለህዝቦች ሁሉ ዓአ ቤክ የወላጆች ሥልጠና

2ኛ ለወጣቶች ጽሑፍ መልእክቶች

ለወጣቶች የሚሆኑ አጫጭር በአማርኛና በኦሮምፋ የተዘጋጁ የፌስቡክ መልእክቶች ከኖቬምበር 2019 ጀምሮ መለጠፍ ተጀምሯል:: መሪ ቃል **በልዩነት የተገለጠ ወጣት** የሚል ነዉ::
በአማርኛ ቋንቋ ለ10 ሁለት ሁለት ሳምንታት በጥቅሉ 20 ሳምንታት ከ November 2019 ጀምሮ እስከ June 2020 (የኮቪድ 19 ወራት ጨምሮ) በፌስቡክ የተለጠፉት የወጣቶች መልእክቶች **በ22071 ሰዎች** ተጎብኝተዋል:: ቀደም ብሎ በ2019 ከነበሩት አራት ሳምንታት በስተቀር ይህ የተከናወነዉ ባብዛኛዉ እአአ 2020 ነዉ::

በፌስ ቡክ መለያ ቁጥሩ FBY #21 የሆነና **በልዩነት የተገለጠ ወጣት መሠረቱ የጠበቀ ነዉ፤** የሚል በሉቃ 6፡46-49 ላይ ተመሥርቶ Jan 9,2020 የተለጠፈዉ መልእክት ከፍተኛዉን እይታ አግኝቷል፤ ማለትም **በ21193 ሰዎች** ተጎብኝቷል::

በተመሳሳይ **በኦሮምፋ ቋንቋ** ቀደም ብሎ ለ5 ሁለት ሁለት ሳምንታት በጥቅሉ 10 ሳምንታት ከ December 2019 እስከ June, 2020 በፌስቡክ የተለጠፉት የወጣቶች መልእክቶች **በ 246 ሰዎች** ብቻ ተጎብኝተዋል:: (ዝርዝር ሪፖርት ተያይዟል)
በጥቅሉ በአማርኛም ሆነ በኦሮምኛ ቋንቋ የተለጠፉ አጫጭር የወጣቶች ጽሑፍ መልእክቶች ከጅማሬዉ **በ22317 ሰዎች** በዲጂታል ተጎብኝተዋል::

ለ. ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ አጠቃላይ ወቅታዊ መልእክቶች

1ኛ በፌስቡክ በቪዲዮ የተለጠፉ ለቤተሰብ ቪዲዮ መልእክቶች (ዋና ዋና ምክረ ሃሳቦች)

ከኮቪድ 19 ወረርሺኝ ጋርና በልጆች ላይ ትኩረት በመስጠት ግለ-ቪዲዮ ቀረጻ (Self Video Recording) በማድረግ የተለያዩ መልእክቶች በፌስቡክና በዩ-ቲዩብ ላይ እየተለጠፉ ይገኛሉ፤ ይህ የተጀመረዉ በሰኔ ወር አካባቢ ሲሆን ሪፖርቱ የሚያተኩረዉ በፌስቡክ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ነዉ::

ኢ የ ሱ ስ ጌ ታ ነ ዉ።

ለ. ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ አጠቃላይ ወቅታዊ መልእክቶች (የቀጠለ)

በወረርሺኙ ምክንያት፤በተለይ አማኞች በቤት ሲቀመጡ ወይም ከቤት ሲሠሩ፣
1ኛ እንደቤተሰብ በህብረት የሚሠሩት ምክረ ሃሳብ (ወደ 18 ነጥቦች)፣
2ኛ አባትና እናት እንደቤተሰብ አባልነታቸዉ በግል የሚያደርጉት ምክረ ሃሳብ፤
3ኛ ወጣቶች እንደቤተሰብ አባልነታቸዉ በግል የሚያደርጉት ምክረ ሃሳብ፤
4ኛ ከአስራ ሶስት ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ልጆች በቤተሰብ እየተመሩ አብረዉ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ምክረ ሃሳብ፣

2ኛ የቤተሰብ ፌስቡክ ቪዲዮ ማጠናከሪያ ጽሑፍ መልእክቶች

2.1 ኢመደባዊ በሆነ መንገድ ከልጆቻችን ጋር የእግዚአብሔርን መልካምነት ስለመነጋገር፣ በዘዳ 6፤ 4-9 እና መዝ 78፤1-30 ላይ የተመሠረተ፤
2.2 የቤተሰብ ማዕድ ገበታ ዙሪያ፣ ከልጆች ጋር ስለሚደረጉ ጭዉዉቶች ማጠናከሪያ ምክረ ሃሳብ የያዘ ነዉ፣ የሐዋ 2፡46፣ ዘፀ 18፣12
2.3 የቤተሰብ ተልእኮ መግለጫ መቅረጽ ዙሪያ የሚያተኩር፣ ማጠናከሪያ ምክረ ሀሳብ ነዉ፤ ሮሜ 12፥ 11፤ ዮሐ 17፡ 4፤ ሉቃ 5፡17-19
2.4 የየዕለት ግል ጥሞና ጊዜ ከጌታ ጋር (Quiet Time) ላይ የሚያተኩር፤ ማጠናከሪያ ምክረ ሀሳብ ነዉ፤ (በክፍል 1 እና 2 ማለትም በሁለት ብሮድካስት የተላለፈ ነዉ)፤ ማር 3፣13-15፤ 1ጢሞ 4፣ 7ለ-8፤ ማቴ 7፣24-27 ላይ የተመሠረተ ነበር።
2.5 ለልጆች ትኩረት በመስጠት በየሳምንቱ እቤት ዉስጥ ስለሚደረገዉ እሁድ አምልኮ ማጠናከሪያ ምክረ ሃሳብ ነዉ፤ (በክፍል 1 እና 2 ማለትም በሁለት ብሮድካስት የተላለፈ ነዉ)፤ ሚልክ 1፣ 7-19፤ ዮሐ 4፣ 21-24 ላይ የተመሠረተ ነዉ።
2..6 እግዚአብሔርን የማይፈራ ትዉልድ እንዳይነሳ ቪዲዮ መልእክት (በ3 ቋንቋዎች በአማርኛ፣ኦሮምኛና እንግሊዝኛ)፣ በመሳ 2፡6-15 ላይ ያተኮረ፤
በድምሩ በዘጠኝ ብሮድካስቶች የተላለፉ ቪዲዮ መልእክቶች **በ 1572 ሰዎች ዲጂታሊ** ተጎብኝቷል።

በተለያዩ ጊዜያት የተለጠፉ ተባራሪ አጫጭር ጽሑፍ መልእክቶች
(በአማርኛና እንግሊዝኛ)
እነዚህ አጫጭር ጽሑፍ መልእክቶች (ጥቅሶች) ከላይ በቪዲዮ የተለጠፉትን የሚያጠናክሩ፣ እንዲደመጡም የሚያነሳሱ ናቸዉ።

3ኛ ሌሎች ጽሑፍ ልጥፎች

ጥቅል የሌጋሲ ፌስቡክ ምልክታዊ ፎቶዎች፣ የድነትና ሌሎች ርዕዮተ ዓለም የሚመለከቱ የተለጠፉ መልእክቶች የብዙ ሰዎች እይታ አግኝተዋል። በድምሩ በጽሑፍ (ቴክሰት) የተለጠፉ መልእክቶች ብቻ በ2557 ሰዎች ደጂታሊ ተጎብኝተዋል።

ከላይ እንደተገለጸዉ በቪዲዮ (1572) ሆነ በጽሑፍ የተላለፉትን መልእክቶች (2557) በዲጂታል የጎበኙ **ሰዎች በድምሩ 4129** ናቸዉ።

በአጠቃላይ ከጅማሬዉ እስከ ጃኑዋሪ አጋማሽ ድረስ የወላጆችና የወጣቶች መልእክቶችን፣ ቪዲዮዎችን፣ አጫጭር ቴክሰት መልእክቶችን በዲጂታል የጎበኙ ሰዎች ቁጥር **50490** ነዉ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

ማስታወሻ፡ ይህ ከላይ የተገለጸዉ በ9791 ሰዎች የተጎበኘዉን የዓመታዊ ጉባዔ እይታን አይጨምርም።

ክፍል ሶስት - ከኮቪድ 19 መከላከል ጋር በተያያዘ ሌሎች ክንዉኖች

በኮቪድ ወቅት ሌጋሲ አባል በሆነበት የተለያዩ የልጆች አገልግሎት ድርጅቶች (ዘጠኝ የምንሆን) ጥምረት፣ ከወርልድ ቪዥን በተገኘዉ ፋንድ፣ ልጆችን ትኩረት ያደረገ፣ ለኮቪድ መከላከል የሚሆን ማስክ፣ ሳኒታይዘር፣ ሳሙና፣ ወዘተ፣ በድህነት ዉስጥ ላሉ ህበረተሰብ ክፍሎች ታድሏል። ማቴሪያሎቹ ተገዝተዉ ለየድርጅቶች የታደሉት አስተባባሪ በነበረዉ በሻሮን ልጆች አገልግሎት ሲሆን አባል ድርጅቶች በየፊናችን በመረጥናቸዉ አካባቢዎች አከፋፍለናል።
በሌጋሲ (እንደ አባልነት) የተመረጠዉ አዳማ ከተማ ሲሆን ተጠቃሚዎች በአዳማ ከሚገኙ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ እንዲመረጡ ተደርጓል። በዚህም የተሳተፉ እያንዳንዳቸዉ በአማካይ ወደ 17 ተጠቃሚዎች አቅርበዉ ወስደዉ አካፋፍለዋል። እነርሱም ገንዳ ጋራ ሙሉ ወንጌል፣ ናዝሬት ሙሉወንጌል ቁጥር 2፣ ሰላም ሠፈር ሙሉ ወንጌል፣ ብርሃነ ክርስቶስ፣ ቃለ ህይወት፣ መካነየሱስ፣ ትንሣኤ ምሥክሮች፣ ገንደ ሃራ ሙሉ ወንጌል፣ ወዘተ ሲሆኑ ከተለያዩ ፈላጊ ህብረተሰብ ክፍሎችም 10 ለሚሆኑ ተከፋፍሏል።

ኢየሱስ ጌታ ነዉ፡፡

ክፍል አራት - የዉስጥ አቅም ግንባታ

ተቀማጭነቱ ላቲን አሜሪካ ከሆነዉና ለችግር ተጋላጭ ከሆኑ ልጆች ጋር በተለይም ቢራዝል ዉስጥ በመሥራት ሆነ፣ በዓለም ዙሪያ ከዚሁ አንጻር በተያያዘ የሥልጠና ሴሚናሮችን በመስጠት ረዥም ዘመን ልምድ ካለዉ መንፈሳዊ ድርጅት ጋር በኢንተርኔት በመገናኘት፣ በኮቪድ-19 ምክንያት እቤት ስንቀመጥ እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም፣ ባዘጋጁት የዌብናር ሥልጠና ላይ መካፈል እንዲቻል መግባባት ላይ መድረስ ተችሏል፡፡ ለዚሁም ግዚአብሔር ሊመሰገን ይገባል፡፡

የዌብናሩ ተካፋዮች የሌጋሲ ፕሬዝዳንትና ሌላ የሌጋሲ መሥራች አባል የሆኑት እህት (የፕሬዝዳንቱ ባለቤት) ነበሩሰ፡፡ የዌብናሩ አደራጆች ተቀማጭነቱ ኔዘርላንድ (ሆላንድ) ከሆነዉ ዩዝ ዊዝ ኤ ሚሽን የሚባል መንፈሳዊ ድርጅት ጋር የተያያዙ ሆኖ እርሱም ካቋቋመዉ ዩኒቬርስቲ ኦፍ ኦል ኔሽንስ (University of All Nations) ከሚባልም ሴሚናሩ እዉቅ የነበረዉ ነዉ፡፡ ዉጤቱም አካዳሚክ ተቀባይነት ያገኘ ነበር፡፡ የዌብናር ሥልጠናዉ ኦን ላይን የተካሄደዉ በሰኔ ወር 2012 (June 15 - 29, 2020) ነበር፡፡ ከ150 በላይ የሚሆኑ የሌሎች ሀገሮች ሥልጠና ተካፋዮች በዌብናሩ ላይ ነበሩ፡፡ መጠነኛ የምዝገባ ክፍያ የተካሄደዉ አሜሪካን ሀገር በሚገኝ የሌጋሲ ደጋፊ የቤተሰብ አባል (ወጣት ባስልኤል ዮሴፍ) አማካይነት ነዉ፡፡

የሥልጠናዉ ዋና ዋና አርዕስቶች ለችግር ተጋላጭ ልጆች (ክፍል አንድና ሁለት)፤ የልጆች ዕድገትና ልማት እንዲሁም ተያያዥ አልሚ እንቅስቃሴዎች፣ ንፅረተ ዓለምና የማህበረሰብ ልማት፣ ናቸዉ፡፡

ክፍል አምስት - እአአ 2020 የሂሳብ እንቅስቃሴና የ2021 በጀት

እአአ 2020 (ጃኑዋሪ እስከ ዲሴምበር) ለዓመቱ ተይ ዞ የነበረው በጀት ብር **ብር 403 000.00** (አራት መቶ ሶስት ሺህ ብር) ሲሆን የዞረዉና የተሰበሰበዉ ገቢ ብር 276200.53 (ሁለት መቶ ሰባ ስድሰት ሺህ ሁለት መቶ ሶስት ከ53/100 ሳንቲም) አጠቃላይ ወጪ ብር 129,179.76 (መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ፣ አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ከሰባ ስድስት ሳንቲም)፣ ነበር፤ ከወጪ ቀሪ ብር 147020.77 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሃያ ብር ከሰባ ሰባት ሳንቲም) ነዉ፡፡ ይህ በኦዲቴር ሊረጋገጥ የሚገባ ነዉ፡፡

እአአ ለ2021 ዓም ለአገልግሎቱ ብር **455,700.00 በጀት** በቦርዱ ታይቶ አልፏል፣ ይህ በጠቅላላ ጉባዔ ወደኋላ እንደሚፀድቅ ይጠበቃል፡፡

ማጠቃለያ

በመጨረሻም አገልግሎቱ በእግሩ እንዲቆም በትጋት ለተንቀሳቀሱ፣ በራቸዉን በመክፈት በትብብር እየሠሩ ላሉ (አአ ዉስጥ፣ ከአአ ዉጭ) አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወጣቶች፣ የፌዴራል መንግሥት ፈቃድ ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንዲቻል ስላደረገ፣ ጥልቅ ምስጋናና ዕዉቅና በዚህም ሪፖርት ይሰጣቸዋል፡፡

እርስዎና ቤተሰብዎም ለዚህ አገልግሎት መሳካት የበኩሎዎን ድርሻ ስላበረከቱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ፡፡

ኢየሱስ ጌታ ነዉ፡፡

መጨረሻ